# የዳዊትን ደም ያንተከተከው ጉዳይ ግራ ያጋባል።

እንዲያው ብዙ ከመሄዴ በፊት ስለዚህ መልዕክቴና ስለማንነቴ ትንሽ ልበል። በዚህ ጽሑፍ ማሳየት የፈለኩት አቶ ዳዊት ከበደ በዶ/ር ታዬ ወደ ቅንጅት መምጣት የተሰማቸውን ስሜት ካነበብኩ በኋላ ብዙ ጥያቄ ስላጫረበኝ እናንተም ትጋሩኝ እንደሆን በማለት ነው።

[የአቶ ዳዊት ከበደን ጽሑፍ ለማንበብ እዚህ የጫኑ](http://www.ethiopianreview.com/2007/jun/Dawit_Kebede_article_06262007.pdf)

http://www.ethiopianreview.com/2007/jun/Dawit_Kebede_article_06262007.pdf

በዕኔ በኩል የዶ/ር ታዬ ወደ ቅንጅት አመራር መምጣት የተሰማኝ ስሜት ግላዊ ስሜት ብቻ ነው። እኔ የቅንጅት አባል ስላልሆንኩኝ ፡ በቅንጅት ፓርቲ የውስጥ ጉዳይ አስተያየት መስጠት አግባብነት አለው ብዬ ስለማላምን ነው። ለዚህ ነው የእኔ አስተያየት ግለዊ ብቻ ነው ያልኩት።

ታዲያ ዛሬ አቶ ዳዊት ባቀረቡት የወቀሳ ጽሑፍ ላይ አስተያየቴን ለኅብረተሰቡ ለማካፋል ምን አነሳሳኝ? መልሱ ቀላል ነው። የአቶ ዳዊት ጽሑፍ ከቅንጅት ፓርቲ የውስጥ ጉዳይ አልፎ መላውን የአገራችንን የፖለቲካ ሁኔታ ገፍቶ ስለሚዳስስ ብቻ ነው።

በመግቢያዬ ላይ እንዳልኩት ዋና ትኩረቴን የማደርገው ከአቶ ዳዊት ከበደ ጽሑፍ ውስጥ ደማቸውን ያፈላውን ጉዳይ ለመመርመር ብቻ ነው። ለአንባቢያን እንዲያመች በማለት ፍሬ ነገር የምለውን ጥያቄ ብቻ እየነቀስሁ ለማሳየት ልሞክር።

1. አቶ ዳዊት ስሜታቸው ተነክቶ በደም ፍላት የጻፉት ጽሑፍ ነውን? <u>መልሴ</u>፡ አዎ ነው። <u>ምክንያት</u>፡ ቅንጅትን ለማፍረስ ብዙ ደክሞ ያልተሳካለትና በኋላም የሕዝብን ድምጽ ክዶ ፓርላማ የገባው ዛሬ ሕዝብ ክህደቱ እያለ የሚጠራውን ሰው ፣ አቶ ዳዊት ከበደ ቃለ ምልልስ ሲያደርጉለት ከተሰነዘረባቸው ወቀሳ ዋናው ለአቶ ክህደቱ ያሳዩት አክብሮትና ትህትና አንዱ ነበር። በወቅቱ የአቶ ዳዊት መልስ፡ 'ነገሩ በጣም አናዶኛል እኔ ግን አንድም የጋዜጠኝነት ሙያዬ በዚህ ላይ እኔ በባህሪዬ የቁጣ ስሜት ማሳየት አልችልበትም ነበር ያሉት። ይህ አባባላቸው በዶ/ር ታዬ ላይ ግን አልሰራም። ቁጣቸው ከሙያቸውም ከተፈጥሮ ወይም የአስተዳደግ ባህሪያቸውም ልቋል።

2. እንደ አቶ ዳዊት አባባል ዶ/ር ታዬ ወደ ቅንጅት ዓለም ዐቀፍ አመራር መምጣታቸው አግባብ ያልሆነበት ብለው የጠቀሷቸው ጉዳዮችስ፡

2.1. የዶ/ር ታዬ የቀድሞ ኢሕአፓነት፡ እውን አቶ ዳዊት ዶ/ር ታዬ ኢሕአፓ እንደነበሩ ማረጋገጥ ይችላሉ? እርግጠኛ ናቸው የሚለውን እንውሰድና ፡ ከዚህ ቀደም ኢሕአፓ መሆን ለቅንጅት አመራርነት የማያበቃ ከሆነ መዘዙ የት እንደሚደርስ አውቀውታል? በቃሊቲም ሆነ በውጪ ያሉ የቅንጅት አመራሮች ይተቹበት።

2.2. የዶ/ር ታዬ የቀድሞ ኢመማነት፡ ይሄስ ወንጀሉ ምኑ ላይ ነው። ወይስ ኢሰመጉን እና ኢነጋማን አይጨምርም? እነ ፕሮፌሰር መስፍን ይመልሱት

3. <u>ግልጽነት፡</u> አቶ ዳዊት ከበደ የቅንጅት ዓለም አቀፍ አመራር የሆኑት ከቃሊቲ በመጣ ውክልና እንደመሆ ሁሉ ዶ/ር ታዬስ ተመሳሳይ ዕድል ቢያገኙ ምን ክፋት አለው።

4. አቶ ዳዊትን ከተፈጥሮ ባህሪያቸው ሁሉ ያወጣቸውና የንዴታቸው መንስዔ ሊሆን ይችላል ቢባል ምናልባት ዶ/ር ታዬ ስለ ምርጫው ሂደትና ስለ ቅንጅት በአውሮፓና በሰሜን አሜሪካ ሰነዘሩዘቸው ያሏቸው አስተያየቶች ይሆናሉ።

4.1. ዶ/ር ታዬ ምጫ ስለመግባትና አለመግባት በሚለው ላይ ያላቸው አቋም፡ አቶ ዳዊት ልብ ካሉት ይህ ጉዳይ ዛሬ ቅንጅትን በውል በመርዳት የሚታወቁት ብዙ ምሁራን ጭምር '' ቅድመ ሁኔተዎች ሳይሟሉ ወደ ምርጫ መግባት አደጋ አለው ብለው ነበር'' ስለዚህ ይህችኛዋ ደም ታፈላለች ለማለት ያስቸግራል።

4.2. ለምርጫው በተደረገ ዝግጅት ቅንጅትን ጨምሮ በርካታ ስህተቶች መፈጸመቸውን ዶ/ር ታዬ መናገሩም እንደ ህጸጽ ተቆጥሯል። ታዲያ አቶ አንዳርጋቸው ጽጌ በሰኔ ወር 1997 ዓ.ም. በቅንጅት ላይ የጻፈው 17 ገጽ ትችት አቶ ዳዊትን ምነው አላስቆጣቸውም።



PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

*4.3 ዶ/ር ታዬ በአውሮፓና በሲአትል በተደረጉ ስሰባዎች ላይ ዶ/ር ብርሃኑ ነጋን እና ብርቱካን ሚዴቅሳን በወያኔ ሰላይነት መፈረጃቸው፡*

እንደ እውነቱ ከሆነ ዶ/ር ታዬ አድርገውት ከሆነ ይህ ከባድ ክስ ነው።

ስለ አውሮፓው ስብሰባ የማውቀው ነገር ባይኖርም በሲአትሉ ስብሰባ ላይ ግን ዶ/ር ታዬ ብርቱካን ሚዴቅሳን በወያኔ ሰላይነት መክሰስ ቀርቶ ስሟን በክፉ ያነሱበት አጋጣሚ አልነበረም። አቶ ዳዊት ማስረጃ ካላቸው ሊያቀርቡ ግድ ይላል።

የአቶ ዳዊት ደም ፍላት ግን መነሻውም መደምደሚያውም ይሄው ይመስለኛል።

ዶ/ር ታዬ በሲአትሉ ስብሰባ ላይ ደጋግመው ደበሎ ለባሽ ይሉ እንደነበረና ይሄ አባባላቸውም ከአንድ ጎራ ቁጣን እንደቀሰቀሰ አስታውሳለሁ። በእርግጥ ዶ/ር ታዬ ቃሊቲ ከታሰሩትም መሃል ወያኔ አስርጎ ያገባቸው ደበሎ ለባሾች መኖራቸውን ተናግሯል።

ዶ/ር ታዬ ከሰባት ዓመት የእስራት መከራው ያገኘውን ልምድ ማካፈሉ እንደ ወንጀል ያስቆጥርበት ይሆን? ወይስ ዶ/ር ታዬ ፈጥሮ ወይም ሰዎቹን ለመወንጀል ሲል የሰነዘረው ቃል ነው። ለመልሱ ሩቅ መሄድ አያስፈልግም። በቅርቡ ከእስር ተፍታ አሁን በውጪ የምትገኘው የቅንጅት አባልና የወጣቶች ኮሚቴ አባል ወ/ሪት ሰርካለም እስር ቤት በነበረችበት ወቅት አብረዋቸው የታሰሩ የወያኔ ሰላዮች እንደነበሩ ፍንትው አድርጋዋለች።

በሲአትሉ ስብሰባ ላይ ዶ/ር ታዬ በወቅቱ በተደጋጋሚ ደበሎ ለባሾችን አጋልጣለሁ ከማለት አልተቆጠቡም ነበር። ይህ አባባላቸው በኋላ በዲሲ በተደረገ ስብሰባ ላይም ተስተውሏል።

ዛሬ ከዓመት ከመንፈቅ በኋላ ይህ አባባላቸው ብዙዎችን እንደገና ድንጋጤያቸውን ያስገረሸባቸው አይመስላችሁም? የሆነ የሚገለጥ ነገር እንደሚኖር አቶ ዳዊትም በመስመር መካከል አስፍረውታል። ልብ ያለው ልብ ይበል።

ጣጣችን ማለቂያው ቅርብ አይመስልም። ግን ሊጠራ ሲል የሚደፈርስ አይነት ነው ብዬ ተስፋ አደርጋለሁ። የትኛውም ትግል ደበሎ ለባሽ ባለበት ለድል በቅቶ አያውቅም። እናም ደበሎን የሚያወልቅ ግርግር አይጠላም ፡ እንዲያውም ለድል ስኬታማነት ብርሃን ነው።

5. ከዚህ በኋላ አቶ ዳዊት የጠቃቀሷቸውን ቅሬታዎቻቸውን ብዙም አልልበትም። እንዲያው እገረ መንገዴን ግን ተጠያቂነት ብለው አቶ ዳዊት ካነሱት አይቀር፡

5.1 አቶ ዳዊት ባለፈው የኢትዮጵያ አዲስ ዓመት ከቃሊቲ መጣ ብለው ስላስተላለፉት የተፈበረከ የኢንጅነር ኃይሉ ሻወል መልዕክት ይቅርታ ጠይቀዋል?

5.2 አፍጋኒስታን የወደቀውን ሄሊኮፕተር ወያኔ ከሶማሊያ ሲዋጋ ሞቃዲሾ የወደቀ የአሜሪካ ሄሊኮፕተር ብለው ስላወጡት የሐሰት ዜና ይቅርታ ጠይቀዋል?

5.3 የትንሳዔ ራዲዮን በሃላፊነት ይሰሩ በነበረበት ወቅት ጎንደር በአርበኞች ግንባር ተያዘ ለሚለው የሐሰት ዜናቸው በኃላፊነት ተጠይቀዋል?

5.4 የአቶ ዳዊት ከበደ የፈጠራ ዜናዎችና የኤልያስ ክፍሌ ወፍ ዘራሽ ወሬዎች ተመሳሳይነትና በወያኔዎች ዘንድ የተቃዋሚ ድረ ገጾችን ቃላባይ ለማድግ ያበረከቱት አስተዋጽዖ አጋጣሚ ወይስ?

በመጨረሻም አቶ ዳዊትን በርቱ ቀጥሉ ነው የምለው። እርሶው ከጀመሩትማ ፈራ ተባ ስንል እስከዛሬ ያመቅናቸውን ሌሎችንም ብዙ ጉዳዮችን ማንሳት ያስፈልግ ይመስለኛል። ነገሮች ካልጠሩ ፡ ተጠያቂነት ከሌለ እና ግልጽነት ከጎደለ ግባችን እየራቀ ይሄዳል። ደበሎ ለባሾች ካለን እርቃናችንን እስክንቀር እንገላለጥ።

ወገኖቼ ከግርግር ሁሉ ይሄኛውን ግርግር አትጥሉት። የጽድቅ ነው።

አርነት አሸናፊ



PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com